በሰጋጅ ፊት የሚያልፍ ሰው በርሱ ላይ ያለበትን ወንጀል ቢያውቅ ኖሮ በሰጋጅ ፊት ከማለፍ ይልቅ አርባ መቆም ለርሱ መልካም ይሆንለት ነበር።

ከቡስር ቢን ሰዒድ እንደተላለፈው: ዘይድ ቢን ኻሊድ አልጁሃኒይ -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- ቡስር ቢን ሰዒድን ወደ አቡ ጁሃይም -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- በሰጋጅ ፊት ስለማለፍ ከአላህ መልክተኛ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈንና - ምን እንደሰማ ሊጠይቀው ላከው። አቡ ጁሃይምም እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ብለዋል: "በሰጋጅ ፊት የሚያልፍ ሰው በርሱ ላይ ያለበትን ወንጀል ቢያውቅ ኖሮ በሰጋጅ ፊት ከማለፍ ይልቅ አርባ
መቆም ለርሱ መልካም ይሆንለት ነበር።" አቡ ነድር እንዲህ ብሏል" አርባ ሲል አርባ ቀን ወይም ወር ወይም ዓመት እንደሆነ
አላውቅም።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ግዴታም ይሁን ሱና ሶላት በሚሰግድ ሰው ፊት ከማለፍ አስጠነቀቁ። ሆን ብሎ ይህንን የሚፈፅም ሰው የሚኖርበትን ወንጀል ቢያውቅ ኖሮ አርባ መቆምን ይመርጥ ነበር። በሰጋጅ ፊት ከሚያልፍ ይልቅ ይህ ይሻለው ነበር። ይህንን ሐዲሥ ያወራው አቡ ነድር እንዲህ አለ: አርባ ቀን ነው ወይስ ወር ወይስ አመት የሚለውን አላውቅም።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/7191